# “ዕቃ-ዕቃ” ጨዋታ የሆነው የኤርትራ ዲፕሎማሲ

**ቶሎሳ ኡርጌሳ**

Utolosa@yahoo.com

አንድ አስገራሚና ቀልድ ቀመስ ዲስኩር ከመሰንበቻው ከወደ ኒውዮርክ ተሰምቷል– በአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ አማካኝነት። የዲስኩሩ ባለቤት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተመድ) የአቶ ኢሳያስ ተጠሪ ናቸው–አምባሳደር አርዓያ ደስታ። ሰውዬው ከአስመራው የሁከት ቡድን መቼ እንደተነገራቸው ባይታወቅም ቅሉ፣ ሰሞኑን በመንግስታቱ ድርጅት አዳራሽ ውስጥ እየተውረገረጉ “በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ተቀባይነት ያለውን የሶማሊያን ፌዴራላዊ መንግስት እንደግፋለን” ሲሉ መናገራቸው በርካታ ሰላም ወዳድ ኃይሎችን ድማሜ ውስጥ ከትቷል። መደመም ብቻ ሳይሆንም፣ ውስጣቸው ንፍር እስኪል ድረስ ሳይስቁ የቀሩ አይመስለኝም። አዎ! በመንግስትነት ተደራጅቶ እንዲህ ዓይነቱን ተራ የልጅ ጨዋታ በዲፕሎማሲ ስም የሚጫወት አካል አስቂኝ እንጂ ሌላ ምን ይባላል።…

…እኛስ ብንሆን እየደነቀንም ቢሆን ለምን አንስቅም?!…አባቴ ይሙት አሁንስ ሻዕቢያ ድርቅናው ብሶበታል፡፡ እስቲ አሁን ምናለበት ኤርትራ ውስጥ ያሉትም ይሁኑ ከኤርትራ ውጪ የምንገኝ ሰዎች በሳቅ ብዛት ልባችን ደክሞ እንድንታመም ባያደርጉን?!… ወቸው ጉድ !…“ወደው አይስቁ” አሉ የመንደራችን አዛውንት አባባ ወርቁ፡፡ መቼም ቢያመንም እንሳቀው እንጂ ሌላ ምን እናደርጋለን?…ታዲያ ውድ አንባቢዎቼ በድራማ ላይ ድራማ እየፈጠረ የሚሄደውን የሻዕቢያ የልጅ ጨዋታ ቀልድን ሰምታችሁ ላለመሳቅ ጥረት ታደርጋላችሁ ብዬ አልገምትም– ነገሩ የሀገራችን ሙስሊም ‘አጃኢብ!’ እንደሚለው ዓይነት ነውና፡፡ ሆኖም እኔም በተቻለ መጠን ሁለት እጆቼን አፌ ላይ ከድኜና አምባሳደሩ “በኮሜዲያንነት” ላላቸው ብቃት እንዲሁም ለፈረበኩት የፈጠራ “ጨዋታ” ያለኝን አክብሮት ሳልገልፅላቸው አላልፍም።…ቂ.ቂ.ቂ….

…እርግጥ የአምባሳደሩ ንግግር የኤርትራ መንግስት እንደተለመደው ዛሬ የተናገረውን ጉዳይ ነገ የማይደግመው መሆኑን የሚያመላክት ከመሆኑም በላይ፣ የአስመራው ቡድን በተጣለበት ማዕቀብ ምክንያት የሚይዘውንና የሚጨብጠውን ማጣቱን ጭምር አስረጅ ነው።…እናንተዬ ማን ነበር “የጨነቀው እርጉዝ ያገባል” ያለው?…የሻዕቢያው ልዑክ ወይም ላኪያቸው ይሆኑ እንዴ?…አዎ! ነገሩ እንዲያ ነው። የጨነቀው ግለሰብና ቡድን ብዙ ነገር ሊዘላብድ ይችላል። አይፈረድበትም። ይታዘንለታል።…ግና የአሸባሪዎች አጋፋሪና አስተባባሪ ከሆነው የአቶ ኢሳያስ መንግስት አኳያ ነገሩ ሲታይ አይታዘንለትም–ይታዘንበታል እንጂ። ለምን ቢሉ፣ የአምባሳደር አርዓያ የኒውዮርክ ሰበካ

ነብር ዥንጉርጉርነቱን እንደማይለውጠው ሁሉ፣ የአቶ ኢሳያስ መንግስትም ከውልደቱ ጀምሮ ይዞት የመጣውን ፀረ-ዴሞክራሲያዊነትንና ከፍ ሲልም የአሸባሪዎች አምራችነት ባህሪውን ሊቀይረው የማይችለው የለበጣ ንግግር በመሆኑ ነው።

ለነገሩ ከልምድ እንደሚታወቀው በኤርትራ መንግስትና በሹማምንቶቹ ውስጥ አንድ ያልተፃፈ ህግ አለ–'ለአንድ ሰከንድም ቢሆን እስከጠቀመህ ድረስ ውሸት ከመናገር ወደ ኋላ አትበል' የሚል። እርግጥም ይህ ህግ ከከፍተኛው የሁከት መሪ ጀምሮ እስከ ሳዋው የበታችኛው ወታደራዊ አመራር ድረስ በጥብቅ ገቢራዊ የሚሆን ነው። ከተፃፈው ሻዕቢያዊ ህግ በላይ በየቦታው ኦፊሴላዊ ባልሆነ መንገድ ተፈፃሚ ይሆናል ቢባልም ያስኬዳል። ታዲያ አምባሳደሩ ኒውዮርክ ላይ የተናገሩት አስገራሚ የማደናገሪያ ዲስኩር ድንገት ነሽጧቸው አለመሆኑን በአንባቢዎቼ ዘንድ ልብ ሊባልልኝ ይገባል–ይህንኑ የአስመራውን አሊያም የምፅዋውን ቤተ-መንግስት የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ ለመተግበር እንጂ።

ያም ሆነ ይህ ግን ውድ አንባቢዎቼ እንደምታውቁት የአስመራው ቡድን ላለፉት 22 ዓመታት የአዞ እንባ እያነባ በአንድ ሴንቲ ሜትር እንኳን ድንበር የማይጋራትን ሶማሊያን በተመለከተ "...እኛ የምንደግፈው የነፃነት ሃይሎችን (አል-ሸባብንና ጋሻ ጃግሬዎቹን ለማለት ነው) እንጂ፣ ከውጭ ተሰርቶ የመጣ በዚያች ሀገር የመቋቋም ማንኛውንም መንግስት አይደለም" በማለት ለአሸባሪዎችን ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በማድረግ በሶማሊያ ህዝብ ችግር ላይ ቤንዚን ሲያርከፈክፍ ነበር። ታዲያ ዛሬ ምን ታይቶት ይሆን ከመሬት ተነስቶ "የሶማሊያን ፌዴራላዊ መንግስት እንደግፋለን" የሚለው? ብለን ስንጠይቅ፤ አንድ ዕውነታ ሳይሸፋፈን ፊት ለፊታችን ላይ ድቅን ብሎ እናገኘዋለን– በ"ወዲ አፎም" የኤርትራ መንግስት ዛሬም እንደተለመደው በልጅነታችን ውሸት መሆኑን እያወቅን የምንጫወተውን "የዕቃ-ዕቃ ጨዋታ" ዓይነት ዲፕሎማሲን እየተገበረ መሆኑን።

እርግጥ ይህን ፅሑፍ የሚያነብ ማንኛውም ሰው "ዕውን የኤርትራ መንግስት ዲፕሎማሲ የዕቃ-ዕቃ ጨዋታ ነው እንዴ?' የሚል ጥያቄን ሊያነሳ ይችላል። አዎ! ጥያቄው ተገቢ ነው። ግና የአስመራው ቡድን ነገረ-ስራ ታታሪዎቹ ጃፓኖች "የምትለኝን ነገር እንዳልሰማህ ስራህ ይጮህብኛል" እንደሚሉት ዓይነት በመሆኑ፤ እስቲ ለማንኛውም በተዝታ መልክ ወደ ትናንቱ ተመሳሳይ አስቂኝ "የዕቃ-ዕቃ ጨዋታዎቹ" እናምራና ወደ ዛሬው የጭንቀት ማስተንፈሻ አንድ ዓይነት "የዲፕሎማሲ ስልቱ" እንመለስ።...

**ጨዋታ አንድ–"ድርቅና ረሃብ ያጠቃቸውን ሶማሊያውንን እንረዳለን!"**

ከምሬ ነው የምላችሁ-ይኸኛውም ቀልድ አይደለም፡፡ አዎ! ሀገራቱን እንዳሻቸው የሚያጦዟትና 20 የማይሞሉት የአቶ ኢሳያስ ባለሟሎች በ'ካቢኔ' ቅርፅ ተሰባስበው ነው–'እኛ የወዲ

አፎም ጀግኖች ጠግበን ስልምንበላ ለሶማሊያ የድርቅና ረሃብ ሰለባዎች የምግብ ዕርዳታ ለመስጠት ወስነናል’ ያሉት–የዛሬ ዓመት ገደማ። ታዲያ እዚህ ላይ የአስመራው መሪ ያሉትን እንደ በቀቀን የሚያስተጋቡትን እነዚህን ጉደኞች ‘የኤርትራ ህዝብ ነው ወይስ እናንተ ናችሁ ዕርዳታውን የምትለግሱት?’ ብሎ መጠየቅ አይቻልም፡፡ ምክንያቱም በዚያች ሀገር ውስጥ ጠግበው የሚያድሩት እነርሱ እንጂ ወንድም የሆነው የዚች ሀገር ህዝብ አይደለምና፡፡...ልጄ! የኤርትራ ህዝብ ምን በወጣው?! እርሱማ በዚያን ሰሞን ዓለም አቀፉ የምግብ ፖሊሲ ጥናት ቡድን “በአደገኛ የረሃብ ደረጃ እየተጠቃ ነው” ሲል እማኝነቱን ገልጾለታል፡፡

እናም የሻዕቢያኖቹ “ጨዋታ” ምጸት እንጂ ሌላ አይደለም። ምክንያቱም ሌላው ቀርቶ በዚያን ሰሞን የወጡ ዘገባዎች እንደሚያስረዱት ኤርትራ ውስጥ ከ2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ለረሃብና ለድርቅ ተዳርጓል፡፡ ሆኖም በወቅቱ የኤርትራ ማስታወቂያ ሚኒስትር የነበሩትና በአሁኑ ወቅት የስርዓቱን አስከፊነት የማታ ማታ ቢሆንም ተረድተው ከድተው የኮበለሉት አቶ አሊ አብዱ ከአቶ ኢሳያስ እንደተነገራቸው ይህን ሃቅ ወደ ጎን በማድረግ፣ “እንሰጣለን” ያሉት ዕርዳታ ከ20 ከማይበልጡት የሻዕቢያ የካቢኔ አባላት የምግብ ወጪ ላይ የተቀነሰ ለመሆኑና ላለመሆኑ በእርግጠኝነት አልነገሩንም ነበር። ለነገሩ የአስመራ ቱባ ባለስልጣናት በዚህ ምድር ላይ “እውነት” የሚባል ዓለምን የሚያግባባ ነገር መኖሩን ዘንግተውታል። አንድ ቀን እንኳን ሳት ብሏቸው ለሃቅ ቆመው አያውቁም። አዎ! ይህ ድርጊታቸው “ያደቆነ ሰይጣን...”እንዲሉት ዓይነት ስለሆነ ምናልባትም ሳት ብሏቸው እውነትን ቢናገሩ በስቅታ መታመማቸው የሚቀር አይመስለኝም፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን፣ ዕርዳታው ከአቶ ኢሳያስ ካቢኔ ተብዬዎች የሀገር ውስጥ ዝርፊያ ተቀንሶ ይሰጥ ቢባል እንኳን “ቱባ ባለስልጣናቱ” ምን ያህል ሊለግሱ ይችላሉ? – እንዲያው ሻዕቢያ በሰዎች ስቃይ ለመቀለድ ካልፈለገ በስተቀር። እንደ እውነት ከሆነ ከሰብዓዊ ስሜት በመነጨ ሁኔታ ዕርዳታ መስጠት የተቀደሰ ተግባር ነው፡፡ የሻዕቢያው ጨዋታ ግን “የምትበላው የላት፣ የምትከናነበው አማራት” ከመሆን ባለፈ፣ አል-ሸባብን በየጊዜው በማስታጠቅ ንፁሃን ሶማሊያዊያንን በተዘዋዋሪ መንገድ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ እያስጨፈጨፈ እንደምን “ሰብዓዊ” ሊሆን እንደሚችል ለራሱ በአስመራው አስተዳደርም ቢሆን ግልፅ የሚሆንለት አይመስለኝም፡፡

ሌላው ቀርቶ ‘ሻዕቢያ ከዚህ ተፈጥሮአዊ ባህሪው ወጥቶ በረሃብ ለተጎዳው የሶማሊያ ህዝብ ዕርዳታ ይሰጣል’ ብለን በየዋህነት ብናስብ እንኳን፣ ‘የሶማሊያን ህዝብ በመወከል ዕርዳታውን የሚረከበው ማነው?’ የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም፡፡ እንደሚታወቀው የኤርትራ መንግስት ደም የጠማው በመሆኑ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ላለው ለሶማሊያን መንግስት ዕውቅና ከመስጠት ይልቅ፣ ከአሸባሪው አል - ሸባብ ጋር ሽር ጉድ እያለ ነው፡፡ እናስ የምግብ ዕርዳታውን የሚሰጠው ሞቃዲሾ ለሚገኘው እና ዓለም አቀፍ ህጋዊ ተቀባይነት ላለው መንግስት ነው ወይስ በሶማሊያ በረሃዎች

ውስጥ እየተሽሎከሎከ የወገኖቹን ህይወት ለሚቀጥፈው አል-ሸባብ?—እርግጥም ነገሩ ግልፅ ነው፡፡ ሻዕቢያ በዚያን ወቅት አል-ሸባብ ይገኝበት አካባቢ በድርቅና በረሃብ እንደተጠቃ ያውቃል፡፡ ይህም አሸባሪው ቡድን በምግብ እጥረት ሳቢያ የሁከት ተግባሩን እንዳያቆም አቶ ኢሳያስ በህዝቡ ስም ድጋፍ ሊያደርጉለት ማሰባቸውን የሚያመላክት ነው— አዎ! “በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት” ይሏል ዘግናኝ ሻዕቢያዊ ጨዋታ እንዲህ ነው?!…

## ጨዋታ ሁለት—“ሶማሊያን ለማረጋጋት የሚደረጉ ጥረቶችን እናግዛለን!”

እንደ እኔ ዓይነት የዋህ ሰው ይህን ንዑስ ርዕስ ሲመለከት፤ አባባሉን የገለፀው የመንግስታቱ ድርጅት ወይም ሠላም ወዳድ የሶማሊያ አጎራባች ሀገሮች ሊመስሉት ይችላል፡፡ ታዲያ ይህንንም ጨዋታ የዛሬ ስምንት ወር ገደማ የተናገሩት የአቶ ኢሳያስ ደቀ-መዝሙሮች መሆናቸውን ሲገነዘብ መገረሙ አይቀርም፡፡ ምክንያቱም አባባሉ የሻዕቢያ “ዓይኔን ግንባር ያድርገው” ማንነት የተለመደ መገለጫ  መሆኑን ስለሚረዳ ነው፡፡

ምንም እንኳን ዓለም አቀፉን ማህብረተሰብ የኤርትራ መንግስት ሶማሊያ ውስጥ እያካሄደ ካለው ሰላምን የማወክ ተግባሩ እንዲቆጠብ በተለያዩ ወቅቶች ከማሳሰብ ባለፈ ሁለት ተከታታይ ማዕቀቦችን ቢጥልበትም፤ዛራም ድረስ ሰሚ ጆሮ ሊያገኝ አልቻለም፡፡ እናም የሻዕቢያ ባለሚሎች ዓይናቸውን በጨው ታጥበው እንደ ኮሜዲያን ድራማ መስራትን ስራዬ ብለው ተያይዘውታል፡፡ የሻዕቢያው የያኔው አፈ-ቀላጤ በታዘዙት መሰረት “ሶማሊያን ለማረጋጋት የሚደረጉ ጥረቶች እናግዛለን” ሲሉ መሳለቃቸው የሻዕቢያ ጨዋታ ሌላኛው ክፍል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሻዕቢያውያኑ ቀደም ሲል “በቁጥር አንድ ጨዋታ” ላይ የተናገሩትን “እገዛ” ለማጠናከርም በሚያስገርም ሁኔታ “…ኤርትራ የሶማሊያ ህዝብ ሉዓላዊነቱን እንዲቀዳጅ፣ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት እንዲጠናከሩ ወዘተ. ጥረት ታደርጋለች፡፡ ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በላይ በቋሚነት ስንከተለው የነበረውም ምርጡ አካሄድ ይኸው ነው፡፡…” ማለታቸው ሻዕቢያ መቼም ቢሆን ሶማሊያን ከማመስ የማይመለስ ለመሆኑ ትክክለኛ ማረጋገጫ ነው፡፡

እኔ በበኩሌ ሻዕቢያኑ የሚቀዝፉት የውሸት ታንኳ ፈጽፅ ሊገባኝ አይችልም— በየአዳራሹ የሚያደርጓቸው ንግግሮች አንድም ቀን እውነት ሰምቼ አላውቅምና፡፡ እስቲ ይታያችሁ! የአቶ ኢሳያስ የሁከት ቡድን በድንበር የማይገናኛትን የሶማሊያን ሉዓላዊ ግዛት እየጣሰ በአውሮፕላን መሣሪያ ማቀበሉ በመንግስታቱ ድርጅት ገለልተኛ አጣሪ ቡድን አማካኝነት ተረጋግጦ እያለ ነው— የዚያች ሀገር ህዝብ ሉዓላዊነቱን እንዲቀዳጅ እሰራለሁ የሚለው?— ሻዕቢያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያለውን መንግስት ባለመቀበል ነው— “መንግስትና የህዝብ ተቋማት እንዲጠናከሩ ጥረት አደርጋለሁ” የሚለው?— እርግጥም ይህ ዓይን ያወጣ ቅጥፈት ነው፡፡ ምናልባት አቶ ኢሳያስ በሚልኳቸው ሰዎች አማካኝነት ‘የምናገረው በተቃራኒው ነው’ የሚሉን ከሆነ ትንሽ ፈገግ

ልንልላቸው እንችላለን፡፡ አሊያ ግን ሁሉም ሰው እንደ እርሳቸው ጭንቅላቱን ሳያመዛዝን የሚጠቀምበት ከመሰላቸው መሳሳታቸውን ማወቅ ይኖርባቸዋል ባይ ነኝ፡፡

ኧረ ለመሆኑ ‘ላለፉት ሁለት አስርታት በቋሚነት የተከተልነው ምርጥ አካሄድ’ ማለት ለአስመራው የሽብር ቡድን ከቶ ምን ይሆን?– ሁከት ወይስ ትርምስ?– እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ዓለም ሻዕቢያን ላለፉት 22 ዓመታት የሚያውቀው የምስራቅ አፍሪካን ሀገራት ለማሸበር በሚያካሂደው የሁከትና የትርምስ ፖሊሲው ነው፡፡ እናስ ይህ አካሄዱ ነው “ምርጥ” የተባለው?–እናተዬ ጉድ እኮ ነው!…ለመሆኑ “የሽብር ምርጥ” ምን ዓይነት ይሆን?– እርግጥ ይህ ጥያቄ ለእኔና ለውድ አንባቢዎቼ ከባድ ይሆናል– ለምን ከተባለ፣ ምላሹን ለማግኘት እንደ አቶ ኢሳያስ የአሸባሪዎች ቡድን ፊታውራሪ እንዲሁም ተግባሩን ከከወኑ በኋላ በፈጣጣነት ኮሜዲያን ሆኖ መጫወትን ስለሚጠይቅ ነው፡፡

**ጨዋታ ሶስት–“ስለ ሶማሊያ እውነት ስለተናገርኩ ቴሌቪዥኔ ሊታገድ ነው!”**

እነሆ ሻዕቢያ ለኤርትራ ህዝብ እየተናገረ ነው–የዛሬ ዘጠኝ ወር ገደማ። እንዲህም አለ– “…የዓለም አቀፉ ማህብረሰብ፣ በተለይም የአሜሪካ መንግስትና አጋሮቹ የኤርትራን የመገናኛ ብዙሃን ሊያግዱቸው እየተሯሯጡ ነው፡፡ ይህንንም እያደረጉ ያሉት በተለይም በሶማሊያና በአካባቢው ጉዳይ ‘እውነትን ብቻ እየዘገበ ያለው’ የኤርትራ ቴሌቪዥን ውሸታቸውን ለዓለም ህዝብ ስላጋለጠባቸው ነው።…”

ይህንን አባባል የሚያነብ ሰው መጀመሪያ ላይ ዓይኑን ለማመን ይቸገር ይሆናል፡፡ ኋላ ላይ ግን ወደ ዕውኑ ዓለም ሲመለስ፣ የአስመራው መንግስት የውሸት ጨዋታ የማይሰለቸው “የጥሬ ፕሮፓጋንዳ” ባለቤት መሆኑን መገንዘቡ አይቀርም፡፡ እርግጥ የኤርትራ ቴሌቪዥን በየትኛው ዘገባው የዓለም ማህብረሰብ ሊያግደው እንደሚፈልግ እንኳንስ ለአንባቢዎቼ ቀርቶ፣ የድራማው ባለቤት ለሆኑት ለአቶ ኢሳያስም ግልፅ የሚሆን አይመስለኝም – እንደለመዱት ዓይናቸውን በጨው ታጥበው መሳቂያ ለመሆን ካልፈለጉ በስተቀር፡፡

እንደሚታወቀው የሻዕቢያው የውሸት ማቀነባበሪያ ቴሌቪዥን እንኳንስ እውነትን ሊዘግብ ቀርቶ “እውነት” ምን እንደሆነ ሰምቶም የሚያውቅ አይመስልም፡፡ ውድ አንባቢዎቼ እንደምታውቁት፣ ቴሌቪዥኑ ሌላው ቀርቶ የግብፅን አብዮትና የቀድሞው የሀገሪቱ መሪ ሆስኒ ሙባረክ በቃሬዛ ፍርድ ቤት እንደሚመላለሱ አያውቅም፡፡ የሊቢያ ህዝባዊ ማዕበል የቀድሞውን አምባገነን መሪ ኮሎኔል ሙኣመር ጋዳፊን (ነፍሳቸውን ይማረውና) እንደ ጠራረጋቸውና ለህለፈተ - ህይወት እንደዳረጋቸው አይቶ እንዳለየ ያለፈ ነው፡፡ ታዲያ ለሻዕቢያ ቴሌቪዥን የሙባረክ ፍርድ ቤት መመላለስና የጋዳፊ ከስልጣን መውረድና መሞት እውነት አይደለምን?– እውነት ካልሆነስ፣

መቼ ነው 'እውነት ነው' ብሎ ለህዝቡ የሚያቀርበው?– የምፅዓት ቀን ወይስ…?–ድንቄም እውነት ዘጋቢ ቴሌቪዥን።

የሻዕቢያ ቴሌቪዥን በሶማሊያም ይሁን በአካባቢው ጉዳይ ተግባሩ እውነትን መዘገብ ሆኖ አያውቅም፡፡ ከዚህ ይልቅ የመሪው ማደናገሪያ ማሽን በመሆን ያለ ሃፍረት የሚሰራ ጣቢያ ነው፡፡ በመሆኑም በዚያን ሰሞን በኮሎኔል ጋዳፊ ሞት ምክንያት ሐዘን ላይ የተቀመጡት አምባገነኑ ኢሳያስ አፈወርቂ ለዘለዓለም 'የሚኖሩና የማይበገሩ፣ ዲፕሎማሲያቸው ውጤታማ እንደሆነ፤ ደጋፊዎቻቸው እየበዙ መምጣታቸውን፣ የሚመሯት ሀገር ድርቅም ይሁን ረሃብ የሌለባት እንዲሁም ኢኮኖሚዋ እያደገ ነው' በማለት ያለምንም መሸማቀቅ የሚደሰኩር ነው፡፡

ሃቁ ግን የሻዕቢያው ቴሌቪዥን እንደሚዘላብደው አይደለም፡፡ አቶ ኢሳያስ የኤርትራ ህዝብ ይሁንታ ከስልጣናቸው ሊወገዱ የሚችሉ ከመሆናቸውም በላይ፤ በሚከተሉት የጠብ-አጫሪነት ፖሊሲ በግንባር ላይ በጀግናው መከላከያ ሠራዊታችን ቅሌትን የቀመሱ፣ በተለያዩ ጎረቤት ሀገራት በፍርድ ቤትም ይሁን በሽምግልና የውርደት ካባን የደረቡ እንዲሁም በዓለም አቀፉ ማህብረሰብ ሁለት ማዕቀቦች የተጣለባቸው የሁከት መሪ ናቸው፡፡ በዲፕሎማሲው ረገድም ቢሆን፤ ሀገራቱን እንደ ደሴት ለብቻዋ ነጥለውና በጎረቤቶቻቸውና በዓለም አቀፉ ማህብረሰብ ዘንድ "ዓይንህን ላፈር" የተባሉ ግለሰብ መሆናቸው ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም፡፡

በደጋፊ በኩልም ቢሆን አቶ ኢሳያስ የገዛ ህዝባቸው ማንነታቸውን አብጠርጥሮ በማወቁ አንቅሮ የተፋቸው በመሆናቸው ሊኩራሩ የሚገባቸው ግለሰብ አይደሉም፡፡ ሰውዬው ሀገር ውስጥ ያለው ህዝብ "ማምሻም ዕድሜ ነው" በማለት አንገቱን ደፍቶ የሚኖርባትን እንዲሁም በለስ የቀናው እርሳቸውን ፍራቻ ወደ ጎረቤት ሀገሮች ጥለዋት የሚሸሿት ኤርትራን የፈጠሩ ከሆናቸውም በላይ፤ ውጭ የሚኖረውም ዜጋ ባያቸው ቁጥር በጥላቻ ታፍኖ ሠላማዊ ሰልፍ የሚወጣባቸው ናቸው፡፡ ለዚህም የዛሬ ስምንት ወር ገደማ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ኤርትራዊያን የአቶ ኢሳያስን በመንግስታቱ ድርጅት 66ኛ መደበኛ ጉባዔ ላይ መገኘትን አስመልክተው ያደረጉት ሰላማዊ ሰልፍን በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህን ተከትሎም በተለያዩ ጊዜያት በሀገር ውስጥ በህዝባቸው ላይ በሚፈጽሙት አፈና እና ግድያ ሳቢያ፤ የመንግስታቱ ድርጅት ከዓለማችን ኋላ ቀርና ጨቋኝ ለሆኑት የአስመራው መሪ ሁኔታውን እንዲያሻሽሉ ማሳሰቢያ እስከ መስጠት ደርሷል–ሰሚ የለም እንጂ።

ታዲያ እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ፤ የሻዕቢያው ቴሌቪዥን ከዚህ ተቃራኒ የሆኑ የውሸት ክምርና ከአቶ ኢሳያስ ስብዕና ጋር አብረው የማይሄዱ ወሬዎችን እየለቃቀመ በማቅረቡ እንደምን "እውነት ዘጋቢ" ሊባል ይችላል?-ኧረ በፍፁም፡፡ እርግጥ ሻዕቢያ እንደለመደው "ከምስራቅ አፍሪካ አንደኛ እኔ ነኝ" የሚለውን 'የልብ እንቅርትን ይመኛል' ፍላጎቱን በህልም ዓለም ለማሳካት፣

ቴሌቪዥኑን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመልካች ያለውና ‘የትኛውም የዓለም ሚዲያ አይደርስብኝም’ የሚል በእውኑ ዓለም በሌለ ጉራውን ለመነስነስ ደፋ ቀና ማለቱ የሚገርመን አይሆንም፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ “ከእኔ በላይ ላሳር” ዲስኩር አቶ ኢሳያስንና ጀሌዎቻቸውን ሳህል ተራራ ከነበሩባቸው ጊዜያት አንስቶ እስከ አሁን ድረስ ጀምሮ የተጣባቸው ተውሳክ በመሆኑ ነው፡፡

የአል -ሸባብ ዜና እና ብስራት ማወጃ ጣቢያ ይመስል በየጊዜው የአሸባሪ ቡድኑን ድል የሚያስተጋባውንና ስለ ተገደሉ፤ ፈነዱ፣ ተጥለቀለቁ… ወዘተ. የመሳሰሉ እንዲሁም እርባና የሌላቸውን ዝባዝንኬ በመለፈፍ የሚታወቀው የአቶ ኢሳያስ ቴሌቪዥን በሀገሩ እንዳይሰራጭ የሚያግድ ስራ ፈት ሀገር አለ ብሎ ማሰብ ሃቁን አለመረዳት ነው፡፡ እናም የአቶ ኢሳያስ መጋለቢያ ፈረስ የሆኑት የካቢኔ አባላት ‘ኤርትራ ለኃያላን ሀገር እንኳን አትመለስም’ በማለት ፕሮፓጋንዳ የሰሩ መስሏቸው “ቴሌቪዥናችን በኃያላን ሀገራት ሊታገድ ነው” የሚል የህጻናት “ዕቃ-ዕቃ” ጨዋታ ዓይነት ያፈጠጠና ያገጠጠ ውሸትን ለህዝባቸው ቢቀላምዱም፤ ሃቁ ግን የዲስኩራቸው ታዳሚ የሆነው የዚያች ሀገር ዜጋ በሻዕቢያ ቅጥፈት የተማረረ ስለሆነ እውነታውን አብጠርጥሮ ያውቀዋል፡፡…

እናንተዬ ነገሩ እንዴት ነው?– እስቲ ይታያችሁ እነ አሜሪካ አብዛኛው ክፍሉ ትግርኛ የሆነውን የኤርትራ ቴሌቪዥንን ሀገራቸው ውስጥ እንዳይሰራጭ ሲሯሯጡ!… ኡኡቴ! ውሸት ማለት እንዲህ ነው እንዴ?– “ሲወራ ሰምተሻል” አሉ እማማ ይመኙሻል፡፡ እንኳንስ አሜሪካና አጋሮቿ ዓለም አንቅሮ የተፋቸውን ኢሳያስን የሚያወድስና ስለ ሶማሊያና አካባቢው “ጦር አውርድ” የሚል ዘገባ የሚያቀርበውን ብሎም ማንም የማያዳምጠውን የሻዕቢያ ቴሌቪዥን ሊያግዱ ቀርቶ፤ ትግሪኛ ቋንቋ በደንብ በሚሰማባት ሀገራችን ውስጥም ቢሆን የአስመራው በሬ ወለደ ቴሌቪዥን እንደ ልብ ማየት ይቻላል– ውሸቱ ስለሚታወቅ ማንም ሊሰማው አይፈቅድም እንጂ፡፡

ታዲያ ከመሬት በመነሳት “የአቶ ኢሳያስን ‘ቴሌቪዥናችን ሊታገድ ነው’ ድራማዊ ጨዋታ እንደ ክበበው ገዳ እና ፍልፍሉን የመሳሰሉ የሀገራችን ኮሜዲያኖች ቢሰሙት፤ እንዴት አድርገው አቀነባብረው ይሰሩት ይሆን ?!” ስል አንድ ወዳጄን መጠየቄ አልቀረም። እርሱም እንዲህ አለኝ– “ማንኛውም ኮሜዲያን የሚሰራው የገሃዱ ዓለም ነፀብራቅ የሆነውን እውነተኛ ድርጊት እንጂ ፈጠራን አይደለም፡፡ ሰውዬው ከማሳቃቸው በስተቀር ልቦለድ ደራሲ ናቸው፡፡”…እውነትም ደራሲ– የውሸት ጨዋታ ደራሲ፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን የአስመራው የቅጥፈት ባለሟል “በሶስት የዕቃ-ዕቃ የዲፕሎማሲ ጨዋታዎች” ሰለማይመለሱ ወደ ሰሞነኛውና አራተኛው የህፃን ልጅ የዲፕሎማሲ ተረታቸው እንዲህ ልውሰዳችሁ።…

**ጨዋታ አራት–“የሶማሊያን ፌዴራላዊ መንግስት እንደግፋለን!”**

የኤርትራ መንግስት ሰሞኑን በአደገኛ ፖለቲካዊ አጣብቂኝ ውስጥ መግባቱን የሚያመላክት ነው–አምባሳደር ኣርአያ ደስታ በኒውዮርኩ የመንግስታቱ ድርጅት መደበኛ ጉባዔ ላይ ያሰሙት ይህ "የዕቃ-ዕቃ ጨዋታ" ዲፕሎማሲ። እንደሚታወቀው ባለፉት ጊዜያት የአቶ ኢሳያስ መንግስት የምዕራቡን ዓለም ትኩረት ለመሳብ በዓረቡ ዓለም ለሽብር ስራው ሲያገኝ የነበረውን ድጋፍ በማፈላለግ ስራ ላይ ተጠምዶ ነበር፡፡ ለዚህም አል-ሸባብ በተለያዩ ከባቢዎች ጥቃት እንዲፈጽም አድርጓል፡፡ በኢሳያሳዊያን አስገራሚ ቀመር መሰረት "አል-ሸባብ ከአል-ቃዒዳ ጋር ግንኙነት ስላለው፣ ዓለም አቀፉ የፀረ-ሽብርተኝነት ጥምረት ኤርትራን በአጋዥነት ሊወስድ ይችላል፤ በዚህም በርካታ ገንዘብ ማግኘት እንችላለን የሚል የተሟጠጠ ተስፋን በስሌትነት ይዞ ተንቀሳቅሷል፡፡

ይሁንና የምዕራቡ ዓለምም ይሁን ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አቶ ኢሳያስንና መንግስታቸውን ከነመፈጠራቸው ረሳቸው። ከእርሳቸው የዜሮ ድምር ጨዋታ ይልቅ ሁለት ማዕቀቦችን በጌጥ መልክ አንገታቸው ላይ አንጠለጠለላቸው። ይህም በሻዕቢያ ምክንያት በቁልቁለት ሽምጥ ግልቢያ ተንደርድሮ ባዶ የቀረውን የኤርትራን ኢኮኖሚ ከድጡ ወደ ማጡ ከተተው። አቶ ኢሳያስም ለአሸባሪዎች የሚደጉሙት ገንዘብ እንዲያጥራቸው አደረገ። እናም ለጊዜውም ቢሆን ፋታ ለማግኘት ሲሉ የተለመደውን የህፃን ልጅ ጨዋታ በመንግስታቱ ድርጅት አዳራሽ ውስጥ በአምባሳደር ኣርአያ ደስታ አማካኝነት እንዲደሰኮር አደረጉ።

ታዲያ ይህ የኤርትራ መንግስት ወቅታዊ አቋም ሻዕቢያ ላለመሞት እየተንፈራገጠ መሆኑን የሚያመላክት እንጂ እውነትም የሶማሊያን ፌዴራላዊ መንግስት ለመርዳት ታስቦ አይደለም፡፡ የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር "አንቺው ታመጪው፣ አንቺው ታሮጪው" እንዲሉ፤ ትናንት አሸባሪዎችን መርጦ "የምደግፈው አል-ሸባብን ነው" በማለት አስመራ ላይ እንዳልከተመ ሁሉ፣ ዛሬ ደግሞ በዚያው አፉ "የሶማሊያን ህጋዊ መንግስት እንደግፋለን" ማለቱ የተለመደው የቅጥፈቱ አካል መሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም፡፡ እርግጥም የአስመራው የሁከት ቡድን ከሽብርተኝነት ስራው በዲስኩር ተማፅኖ የሚላቀቅ አይደለም፡፡ ምክንያቱም አሁንም ቢሆን ከተጠናወተው የትርምስና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ተግባር አለመላቀቁና ወደፊትም ይላቀቃል ተብሎ ስለማይታሰብ ነው፡፡

ለነገሩ የሻዕቢያው መንግስት ላለመሞት የሚንፈራገጥበት "የጣር አካሄድ" የማምታታትና የማደናገር ስልትን የሚከተል በመሆኑ፣ መንፈራገጡ ከመላላጥ ውጭ ጠብ የሚያደርግለት አንዳችም ነገር የለም፡፡ የሰሞኑ የውሸት ዲፕሎማሲውም "ምናልባት ድራማዬ ተቀባይነት ካገኘ የተጣሉብኝ ማዕቀቦች ሊነሱልኝ ይችላሉ፣ ይህም ጊዜ መግዣ ይሆነኛል" ከሚል ቀቢፀ -ተስፋ የመነጨ እና ጭንቀት የወለደው ድርሰት በመሆኑ፤ ምንም ዓይነት ግምትም ሆነ ትኩረት የሚሰጠው አይደለም፡፡ …ግና ሻዕቢያውያን እስከ መቼ ድረስ በስተርጅናቸው ዓለም የሚያውቅባቸውን የህፃን ዲፕሎማሲ በመተወን ይቀጥላሉ?–እርግጥም የዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚገኘው መንበረ-ስልጣኑ በማዕቀብና በሌሎች

ውስጣዊ ክስረቶች ምክንያት እየተነቃነቀ ባለው በአቶ ኢሳያስ መንግስት አመለካከት ውስጥ ብቻ ነው። እኔ ግን ሻዕቢያዊያንን “ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ፣ አሊያ ግን ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል” የሚለውን ብሂል እያስታወስኳቸው ፅሑፌን ልቋጭ። ቸር እንሰንብት።